# ትዝብት ቁጥር 12

## ግንቦት 10-2002 ዓ.ም(18-05-2010)

ለአለፉት ዓመታት እንዳደረኩት ዘንድሮም ወደ ኢትዮጵያ ብቅ ብዬ ከስድስት ሳምንታት ቆይታ በኋላ ወደ ምኖርበት አገር ከተመለስኩ ይኸው ሁለት ቀን ሆነኝ።ምንም እንኳን በመጨረሻው ቀን ላይ የለከፈኝ ጉንፋን ፋታ ቢነሳኝም በቆየሁበት ጊዜ ያየሁትንና የሰማሁትን በትዝብት አምድ ላይ አስፍሬ ለአንባቢያን ለማካፈል የገባሁት የውዴታ ግዴታ አለብኝ ብዬ ስላመንኩኝ የተገነዘብኩትን አጠር መጠን አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ። የግል አስተያየቴን በመጨመር አንባቢያን ለሚመስላቸው መደምደሚያ ነጥብ ላይ ለመድረስና ለሀሳብ ልውውጡ በር ሊከፍት ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

በተለመደው የአየር ጉዞ ወደ ኢትዮጵያ የተጓዝኩት ቅዳሜ እለት ሚያዝያ 2-2002 ዓ.ም ነበር።የተሳፋሪው ቁጥር እንደበፊቱ ብዙ አለመሆኑን የአውሮፕላኑ ወንበር ክፍተት ያሳያል።

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ በርቀት ጭል ጭል እያለ ይታየን የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ የጎዳና መብራት ለማረፍ ዝቅ እያልንና እየተቃረብን ስንመጣ በመጠኑም በድምቀቱም እየጨመረ መታየት ጀመረ።ከአምስት ደቂቃ በኋላ የአውሮፕላኑ ጎማ መሬቱን ሲነካ በሰላም መግባታችንና ማረፋችን ተረጋገጠ።

በቪዛ ቁጥጥርም ሆነ በዕቃ መረከቢያውና ማስፈተሻው ቦታ ምንም አይነት ችግርና ውጣ ውረድ ሳይኖር በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሳፋሪው የእንግዳ መቀበያ አዳራሹን እየለቀቀ በየአቅጣጫው አመራ።

እንደተለመደው ወደ ቤተሰቦቼ ቤት የሄድኩት በኮንትራት ታክሲ ነበር፤ምንም እንኳን የነዳጅ ዋጋ ጣራ ቢነካም በክፍያ በኩል በተለይም እንደኔ ላለው የውጭ ነዋሪ የሚጎዳና የሚቆረቁር አልነበረም።በጉዞ ላይ በአሁኑም እግሬ ግማሽ ጨለማ ግማሽ መብራት ያለበትን ሰፈር እያቋረጥኩ ነበር ከቤት የደረስኩት። ከስምንት ወር በፊት የነበረው ችግር ሳይወገድ በቀጣይነት የመብራት ወረፋ እንዳለ በማግኘቴ ግር ቢለኝም ምክንያቱን ለማወቅ ጉጉት አላደረብኝም ነበር፣ ምክንያቱ ያው ስለነበር መፍትሄው እስኪገኝ ድረስ እንደ ህዝቡ በትእግስት ከመጠበቅ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን በመረዳት አስተያየት ለመስጠት እንኳን የሚቻልበት ሁኔታ ባለመኖሩ ስሜቴን ዋጥ አድርጌ ከመቆየት ሌላ ምርጫ አልነበረኝም።ሕዝቡም ችግሩ አብሮት ስለከረመ ሁኔታው ቢያበሳጨውም ሌላ ምርጫ ስለሌለው ከሚሰጠው አስተያየትና የብሶት ቃል ያለፈ አቅምና መፍትሄ አላገኘለትም።

የነበርኩበት ወቅት የሚያዝያ ወር ቢሆንም የነበረው የአየር ጸባይ ግን ከክረምቱ የባሰ ነበር፤በአዲስ አበባና በሌሎቹም ያገሪቱ መካከለኛ ክፍሎች ያለማቋረጥ ከፍተኛ ዝናብ

ሲጥል ሰንብቷል።የዝናቡ ስርጭት ወደ ግንቦቱ ወር በመሻገር በተለምዶ ከፍተኛ ሙቀት ይታይበት የነበረው የበጋው መጨረሻ ወር ጎርፍና ነጎድጓድ ያካተተ፣ፀሃይና ደመና የሚፈራረቅበት፣ሞቅ ብሎ የሚበርድ ቅጡ ያልታወቀ የአየር ጠባይ የሚታይበት ጊዜ ነበር።የዝናቡ ክብደት ለአንዳንድ የእርሻ ምርቶች ጎጂ ቢሆንም ለመስኖና ለክረምት አዝእርት /ለጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ/ ከተጠቀሙበት ጥሩ አጋጣሚ ነው።

## የኤኮኖሚ ሁኔታ

በተከሰተው የኤሌክትሪክ ሃይል ችግር ሳቢያ በአገሪቱ ውስጥ የተጀመሩት የግንባታ ስራዎች ፣የቤትና የመንገድ ግንባታዎች እንዲያዘግሙ ወይም እስከነጭራሹ እንዲቆሙ ሆኗል።ከነዚሁ ልዩ ልዩ ግንባታ ስራዎች ጋር የተያያዙት የልዩ ልዩ ድርጅቶች ስራና እንቅስቃሴ አብሮ በመዳከሙ ወይም ከነጭራሹ በመቆሙ ለብዙ ሰራተኞች ከስራ መባረርና ለችግር መጋለጥ ምክንያት ሆኗል።

ይህ ችግር በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ለብዙ ትችት የዳረገው ሲሆን ለተቃዋሚ ድርጅቶችም አንዱና ዋናው ማጋለጫ ነጥብ ሆኖላቸው ከርሟል።በተለያዩት ያገሪቱ የሃይል ማመንጫ ግንባታዎች ስራ በተጠናቀቀባቸው ግድቦች የሚገኘው አዲስ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ የአገሪቱን ችግር ሙሉ ለሙሉ ያሶግዳል ባይባልም በከፊል ችግሩን ሊቀርፍ እንደሚችል ግን አይካድም።ሰሞኑን የተመረቀው የበለሳ ግድብ ሃይል ማመንጫና በተከታታይ ስራቸው ተጠናቆ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ግድቦች ጥምር ሃይል ብቃት ሁለት ሽህ ሜጋ ዋት እንደሚደርስ ቅድመ ጥናቱ ያመለክታል። ይህም ሆኖ የአገሪቱን ፍላጎት ለማሟላት የብዙ ግድቦች ግንባታ እንደሚያስፈልግ ባለሙያዎች ይናገራሉ።ከግድቡ ግንባታ  ጎን ለጎን አብሮ የሚያሳስበው ሌላው ጉዳይ የውሃው መጠንና ብቃት ነው።በብዙ ወጭ የሚገነቡት ግድቦች በቂ ውሃ ለመረከብ ካልቻሉ ከሚፈለገው ግብ ለመድረስ አይቻልም፣ችግሩም በቀጣይነት ይኖራል ማለት ነው።

በዚሁ በግድብ ስራ ዙሪያ ላይ የተከሰተው ሌላው ችግር ደግሞ የግድቡ ስራ ጥንካሬና ጥራት የሚመለከተው ነው።በግልገል ግቤ ግድብ ስራ ላይ የደረሰው የዋሻ መደርመስ ስራውን ሲያጓትት ለወደፊቱ ለሚኖረው ዋስትና ብዙ ጥያቄዎችን ከማስነሳቱም በላይ መንግስት ለአንድ የጣልያን ተቋራጭ በተለያዩ ቦታዎች ሊሰሩ የታቀዱትን ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች አሳልፎ መስጠቱ ትክክል አይደለም ፣ከሙስና ጋር የተያያዘ አሰራር ነው በማለት የተቃዋሚ ድርጅቶች አድራጎቱን አውግዘዋል።መንግስት በበኩሉ ብድሩ የተገኘው ከጣሊያን ስለሆነ ስራውም ለአበዳሪው አገር ተቋራጭ መስጠቱ ግዴታ ነው፣በተጨማሪም ኩባንያው በተለያዩ አገሮች ውስጥ ተመሳሳይ ስራ የሰራ ፣ልምድና ችሎታ ያለው ነው በማለት ትችቱን ሳይቀበለው ቀርቷል።

በወቅቱ ካለው የኤሌክትሪክ ሃይል ችግር ጋር የተያያዘው የሲሚንቶ አቅርቦት በመቀነሱ የዋጋ ግሽበት አስከትሏል፤የአንድ ከረጢት ሲሚንቶ ዋጋ እስከ አራት መቶ ብር ደርሷል።በዚህ የተነሳ ብዙ ህንጻዎችና ቤቶች በጅምር ቀርተዋል፤በዚያም ዙሪያ የተሰማራው አያሌ ባለሙያና የቀን ሰራተኛ ከስራው ተባሮ ወይም ተቀንሶ ለችግር ተጋልጧል።በሌላውም የስራ ዘርፍ የተሰማራው በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ተዘፍቋል።

ምንም እንኳን መንግስት በተለይም የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ለፓርላማ ስብሰባ የስድስት ወር የስራ ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት ያገሪቱ ኤኮኖሚ በአስራ አንድ ከመቶ እጅ(11%) አድጓል ብለው ለተናገሩት የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና የፓርላማ አባላት የማይመስል ነገር ነው ብለው ቢከራከሯቸውም፣አቶ መለስ ግን ከአቋማቸው ፈቀቅ ሳይሉ ለማሳመን ሞክረዋል።በዚህ ግማሽ ስድብ ግማሽ ዛቻ ባካተተው የአቶ መለስ ሪፖርት በተቃዋሚ ድርጅቶችና በመሪዎቹ ላይ ከምርጫው ዋዜማና በኋላ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ እንደታሰበ ቁልጭ ያለ አመላካች ተስተውሏል።

የውይይቱ አካሄድ አድልኦና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነበር ለማለት ይቻላል።በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ አብዛኛው የፓርላማ ወንበር በስሩ ስለሚገኝ ለውይይት የሚፈቀድለት ሰዓቱም እንዲሁ ከሌሎቹ የላቀ ነበር።ይህ አሰራር ከጀርመን የፓርላማ አሰራር የተወሰደ ነው በማለት ሕጋዊና ትክክለኛ  ለመሆኑ አቶ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ ገልጸውታል። ይህ አሰራር  በፓርላማ የውይይትና የክርክር ወቅት ብቻ የሚከበር ግዴታ ሳይሆን ለምርጫ በቀረቡት ድርጅቶች መካከል በሚደረገው የቴሌቪዥንና የራዲዮ ክርክርና ውይይት ወቅትም በተግባር ተተርጉሟል።ለዚሁ ተግባር ከተመደበው  የአየር ስርጭት ከ60% በላይ የሚሆነው ሰዓት የተመደበለት ለገዢው ፓርቲ ለኢሕአዴግ ነው።

እንደውነቱ ከሆነ ፣ምንም እንኳን ከበፊቱ የተለዩ የብዙ ድርጅቶች ተሳትፎ የሚታይበት የተለያዩ ዘርፍ እንቅስቃሴ መኖሩ ባይካድም የአገሪቱ እድገት ፣የኤኮኖሚ አቅም በአስራ አንድ በመቶ ጨምሯል ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር አይሆንም፤ ምክንያቱም

1ኛ-በማመንጫ ሃይል ድክመት የተነሳ አገሪቱ ለአገር ውስጥ ፍጆታም ሆነ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ምርት በማነሱ

2ኛ.የተጠናቀቁትና የተጀመሩት ታላላቅ ፕሮጀክቶች የቤትና የመንገድ ጭምር የውጭ ካፒታል፣የብድር ገንዘብ የፈሰሰባቸው ባለ ዕዳ ንብረቶች በመሆናቸው በመጀመሪያው ዓመታት የሚያስገቡት ገቢ እንኳን ቢኖር ለእዳ ክፍያ እንጂ ወደ መንግስት ካዝና የሚገባ ባለመሆኑ።

 እንዲሁም የመንገድ መዘርጋት ለልማቱ እንቅስቃሴ እንደዋና አጋዥ የሚቆጠር እንጂ ብቻውን ለአገር ካፒታል ምንጭ አይሆንም።ከመንገዱ ጋር አብሮ መስፋፋት ያለበት የትራንስፖርቱ ተቋምና ታላላቅ የእርሻና የሌላውም ምርት አቅራቢ ድርጅቶች በገጠር በመስፋፋት የአገሩን ፍላጎት አሟልተው ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ የሚያስችላቸው አቅም ገና አልጎለበተም፤ ስለሆነም መንገድ ስለተዘረጋ ብቻ ኤኮኖሚው አድጓል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም።ለኢኮኖሚው እድገት በር በመክፈት ላይ ነው ብሎ ለመናገር ግን ያስችላል።አሁንም የአገሪቱን ገበያ ያጥለቀለቃት የውጭ አገር በተለይም የቻይና ና የአረብ አገር ምርትና የፋብሪካ ውጤት ነው። በመንገዱ መስፋፋት እየታገዘ ለውስጥና ለውጨ ገበያ ምርቱን ሊያቀርብ የሚችል ተቋም ሲስፋፋ ለአገሪቱ ካፒታል መጨመር ምክንያት ይሆናል።

3ኛ.አገሪቱ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ምርት ከውጭ አገር ከምታስገባው ምርት ጋር ስለማይመጣጠን፣የምትገዛው ከምትሸጠው በብዙ እጥፍ ስለሚበልጥ ለውጭ ምንዛሪ ባለእዳ አገር ሆናለች።

4ኛ.የአገር ውስጥ የፍጆታ እቃዎች(የምግብና የመሳሰሉት ሳይቀሩ) አቅርቦት ፍላጎትን ስለማይሸፍን ዋጋው እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም፣ስለሆነም ተጠቃሚው ሕዝብ የገቢ ምንጩ የተወሰነ በመሆኑ የአገር ውስጡን ገበያና ምርት ከመጠቀም ይልቅ የውጭ እርካሽ ሸቀጦችን በመምረጡ የአገር ካፒታሉ እንዳያድግ እንቅፋት ሆኗል።

አፍን ሞልቶ ጨምሯል፣አድጓል ተብሎ ሊነገርለት የሚገባው የማይካደው ነገር ቢኖር የዋጋ መናሩ ብቻ ነው።የማንኛውም እቃ ወይም የእርሻ ውጤት ዋጋ ከሰላሳ ከመቶ በላይ ጨምሯል።የሰራተኛው ደመወዝ ግን ባለበት ይረግጣል። ጭማሪ ተደረገም ቢባል ወጭውን የሚሸፍን አይደለም።የዋጋ ግሽበት ከሰላሳ በመቶ በሆነበት አገር የአስር በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ቢኖር አሁንም ለሕዝቡ የስቃይ ኑሮ ነው። የዋጋ መናር መኖር ደግሞ የእድገት ምልክት ሳይሆን የእጥረት፣ የችግር፣የድህነት፣የውድቀት ምልክት ነው።መንግስት በአንድ በኩል ኤኮኖሚው አድጓል እያለ በሌላ በኩል ከተዘፈቀበት ችግር ለመውጣት ሲል ችግሩን በህዝቡ ትከሻ ላይ ሲያስቀምጥ ይታያል።በቅርቡ የተወሰደው የቫት ክፍያ ግዴታ እርምጃ ለዚህ ዋና ምስክር ነው።በማንኛውም የሆቴል፣የሱቅ፣የምግብ ቤት፣የመጠጥ ቤት፣ የግንባታ፣የማምረቻ ድርጅት...ወዘተ አገልግሎትና የሽያጭ ልውውጥ ዋጋ ላይ ተጨማሪ የአስራ አምስት ከመቶ የቫት ክፍያ በሕግ ተጥሏል።ይህም ተጠቃሚው እንዲታቀብና እንዲያፈገፍግ፣የሻጭና የአገልግሎት አቅራቢው የስራ ዘርፍ እንዲዳከም ብሎም እንዲዘጋ መንገድ ከፍቷል።

የገጠሩ ኑዋሪ ኑሮው እንደተለወጠ ተደርጎ ብዙ ቢወራለትም ኑሮው ያው በገሌ ነው።የአንዳንድ ገበሬ መሻሻልና ስኬት የብዙሃኑን ገበሬ ኑሮ ተሻሽሏል ለማለት አያስደፍርም።አሁንም በአገሪቱ ውስጥ የምግብ እጥረት አለ።አገሪቱ አሁንም የውጭ አገር የምግብ እርዳታ ጥገኛ ነች።በእርግጥ ገበሬው ከችግር ለመውጣት የሚያደርገው ጥረት የሚደነቅ ነው።ተፈጥሮና መንግስት ቢረዳው ኑሮ የት በደረሰ ነበር።የገጠሩ ኑዋሪ አሁንም ለትንሽ ሕክምና ወንዝ አቋርጦ በወሳንሳ መጓዙ አልቀረም ።በክፍለ ሃገር ከተማ ቀርቶ በአዲስ አበባ ከተማ እንኳን የሕዝቡ ጤና ጥበቃ ተቋማት በጣም በሚዘገንን ፣የጽዳት ጉድለትና የመድሃኒት እጦት በዛ ላይ የሃኪሞቹ የንቀትና ግድ የለሽነት ኮስታራ ፊት ሲጨመርበት በበሽታ ላይ በሽታ እንደመጨመር ይቆጠራል።ከየጠቅላይ ግዛቱ ለአነስተኛ ሕክምናና ምርመራ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣውን በሽተኛ ቤት ይቁጠረው ብሎ ማለፉ ይቀላል።በትምህርት መስክም እርግጥ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች መከፈታቸው አይካድም ሆኖም ግን ውስጠ አቅማቸውንና ያዞታቸውን ሲያዩት የአንድ ጠንካራ ኮሌጅ ያህል ጥራት የላቸውም፣ሁሉም ቢጨፈለቁ አንድ ምራቁን የዋጠና የተሟላ ዩኒቨርሲቲ አይወጣቸውም።

አንድ መንግስት ስልጣን ላይ የሚቀመጠው ለመስራትና አገር ለማሻሻል ነው።የመስራትና አገር የመገንባት ግዴታና አላፊነት አለበት።ያንን ካላደረገ ተጠያቂ ነው።ኢሕአዴግም የተሰሩትን ስራዎች እንደ በጎ አድራጎት መቁጠር የለበትም።ሃያ ዓመት ቀርቶ ልስራ ላለ መንግስት አምስት ዓመት ብዙ ሊያደርግ የሚችልበት

የስልጣን ጊዜ ነው።ኢሕአዴግ የመጀመሪያ አስራ ሁለቱን ዓመታት በዋዛ አሳልፎ ያለፉትን ስምንት ዓመታት ለስራ በመነሳቱ እንደተአምር ባይቆጠርለትም እንደተኛ አለመቅረቱ ሊደርስበት የሚችለውን የሕዝብ ቁጣ ሙሉ በሙሉም ባይሆን በጥቂቱ ሳይሸርፍለት አይቀርም።ይበልጥ ለመወደድና ለመፈቀድ ይበልጥ ሕዝቡን ማክበር፣የአገሪቱን ጥቅም አሳልፎ አለመስጠት፣የሕዝቡን ፍላጎትና አንድነቱን ማክበርና ማስከበር፣የዘር ፖለቲካን እርግፍ አድርጎ መጣል ያስፈልጋል።

የተሰሩት ስራዎች ሁሉ በአገሪቱ ሃብትና በሕዝቡ ጉልበትና ግብር እንዲሁም በሚከፈል ዓለም አቀፍ ዕዳ በመሆኑ ማንም ድርጅት ስልጣን ያዘም አልያዘም የሚመጻደቅበት የግል ሃብቱ አይደለም።

በአንዳንድ ቦታዎች የመስኖ እርሻ በመጀመሩ በዓመት ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ምርት ለመሰብሰብ ተችሏል።ሰሞኑን ከዚህ በፊት ታይቶና ተለምዶ የማይታወቅ የበቀሎ እሸት ለገበያ ውሏል።ከመስከረምና ከጥቅምት ወራት ውጭ ለዚያውም በግንቦት ወር በቀሎ እሸት ተጠብሶና ተቀቅሎ ለመግዛት ባይችሉም ማየትና ማሽተቱ አንደ ለውጥ ነው።ሆኖም ግን በዓመት ውስጥ ሁለት ሶስት ጊዜ መመረቱ በተጠቃሚው ወጭ ላይ ያመጣለት ጥሩ ለውጥ የለም።አንድ በቆሎ ሁለት ብር ሲሸጥ ሶስት ከገዙ ግን የአንድ ብር ቅናሽ ኖሮ አምስት ብር ያወጣል። እኔ በአምስት ሳንቲም አንድ በቀሎ የበላሁበትን ጊዜ ሳስበው ህልም ይመስለኛል።በሌላ በሌላውም የምግብና የእርሻ ውጤቶች ላይ ማለትም በእህል ፣በስጋ(አንድ ኪሎ ዘጠና ብር)፣በቅቤ፣ በዘይት፣በመሳሰሉት የሚጠራው ዋጋ ያስደነግጣል፤የሱካርም ዋጋ አንድ ኪሎ ከአስራ ሶስት ብር በታች አይገኝም።ሕዝቡ እንዴት አድርጎ ኑሮውን እንደሚገፋ ሲያስቡት ይገርማል።ብዙሃኑ ሕዝብ እያቃተተ በሚኖርበት የመከራ ኑሮ ኤኮኖሚው አድጓል ብሎ መናገር የሕዝቡን ኑሮ በባለጸጎቹ ኑሮ መነጽር ከማየት አንጻር ካልሆነ በስተቀር ከእውነት የራቀ ነው።

የአንድ አገር ኤኮኖሚ አደገ ሲባል ዋናው መለኪያ የሕዝቡ የመግዛት አቅም ሲጨምር፣ኑሮው ሲሻሻል፣ ጤናው ሲጠበቅ፣ሌላው ቢቀር እንኳን ሊገዛው የሚችለው መድሃኒት በብቃት ሲገኝ፣የከባቢው ጽዳት ሲጠበቅለት፣የአስፈላጊ ነገሮች የውሃና የመብራት አቅርቦት ከወረፋ ሲወጣ፣በአጠቃላይ የኑሮ ደረጃው ሲሻሻል እድገት መጣ ይባላል።ያ ካልሆነ ግን ከተስፋና ከምኞት የተለዬና የራቀ አይሆንም።ሕዝቡ እራሱ ኑሮውን ስለሚያውቀው ዲስኩርና ጫጫታ ሀቁን ሊሸፍነው አይችልም።

በከተማዎች ውስጥ የመኖሪያ ቤቶችና ሕንጻዎች መሰራት የሚካድና የሚነቀፍ ባይሆንም አብዛኛው የተሰራው በባንክ ብድር መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም። ባንኮች ያበደሩትን ገንዘብ ለማግኘት ስለተቸገሩ ለቤት ስራ ላለማበደር ወስነዋል።ታላላቅ ህንጻ የሰሩትም በጣት የሚቆጠሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ናቸው።በከተማና ከከተማ ወጣ ብለው በሚገኙት ዘመናዊ የመዝናኛ ቦታዎችና ሆቴሎች ውስጥ የፈለጉትን የሚያደርጉም መኖራቸው አይካድም፤ግን የእነዚህ መኖር የአዲስ አበባን ወይም የአገሪቱን ሕዝብ ኑሮ መመዘኛና የእድገት ምልክት አድርጎ መውሰድ ከስህተት ላይ ይጥላል።አብዛኛው ያገራችን ሕዝብ ኑሮው ከድህነት ወለል ስር ነው።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በአይስ ላንድ የተከሰተው የሳተ ገሞራ ፍንዳታ /የጭስ ደመና ስርጭት/ አገሪቱ ለውጭ ገበያ በምታቀርበው የአበባ ገቢ ላይ ጠንካራ ክንዱን አሳርፎ ለብዙ ሚሊዮን ኤይሮ ኪሳራ ዳርጓታል።ለገበያ ተዘጋጅቶ የነበረው የአበባ ምርት በበረራ መሰናክል የተነሳ ከታሰበበት ቦታ በተፈለገው ቀንና ሰዓት ባለመድረሱ አምራቾቹን በጣም የጎዳ ሲሆን በሂደቱ በልዩ ልዩ መልክ ከሽያጩ ይገባ የነበረው ያገሪቱ ገቢ ሳይገባ ቀርቷል፤ብዙ ሰራተኞችም በደረሰው ክስረት የተነሳ ገቢ አልባ መሆናቸው በሰፊው ይወራል።

የአገሪቱ ገንዘብ /ብር/ የመግዛት አቅሙ እየተዳከመ በመሂዱ የዋጋ ግሽበቱ በየቀኑ እየጨመረ በመሂድ ላይ ነው።ትናንትና የገዙት እቃ ዛሬ በእሩብና በግማሽ ጨምሮ ይገኛል።የቤትና የቦታ ነገርማ አይነሳ! በዚህና በመሳሰሉት በተለይም በእቃዎችና በሲሚንቶ እጥረት የተነሳ በቤት ስራ ይታይ የነበረው እንቅስቃሴ ሁሉ ተዳክሟል። የተጀመሩት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ስራ ሲጠናቀቅና አቅርቦቱ ሲጨምር  ገበያው ሲረጋጋና የገዥው መንሰፍሰፍ ጋብ ሲል እስከ አሁን ድረስ የተለመደው የሚያስደነግጠው የዋጋ ጥሪ የሚያከትምበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል በማለት ሁሉም በተስፋ ይጠብቃል።ያ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

## በፖለቲካው ዙሪያ

የነበርኩበት ወቅት በቅርቡ ለሚጠናቀቀው ለአራተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅት የሚንቀሳቀስበት ጊዜ በመሆኑ የሚደረጉትን ውይይቶችና የሚቀርቡ ትችቶችን ለመከታተል እድል አግኝቻለሁ።

በዚህ በመጭው ምርጫ ለመሳተፍ ስልሳ ሶስት ድርጅቶች በምርጫ ቦርዱ ተመዝግበው እውቅናን ያገኙ ሲሆን የምርጫ ስነምግባሩንም መፈረማቸው ተረጋግጧል።ሁለት ድርጅቶች ብቻ ሰነዱን አንፈርምም በማለታቸው ከምርጫው ተገልለዋል።በዚህ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ ከቀረቡት አብዛኛዎቹ /ከ90 %/በላይ የሚሆኑት በክልልና በዘር ላይ የተመሰረተ ዓላማና መመሪያ ያነገቡ፣የጠራ የፖለቲካ መስመርና ፕሮግራም የሌላቸው፣የህዝቡን አንድነት ለመከፋፈል ሆን ተብለው የተፈጠሩ መሆናቸውን በሚከተለው ዝርዝራቸው ለማወቅ ይቻላል።ዝርዝሩ በአገር አቀፉ ምርጫ የተመዘገቡትን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በአገሪቱ ውስጥ በስልጣን ላይ ባለው መንግስት መመሪያ ፈቃድና እውቅና የተሰጣቸውን አገር አቀፍ፣ክልል አቀፍና መንደር አቀፍ ድርጅቶችን ያጠቃለለ ሲሆን አገራችንን ወደፊት ምን አይነት መከራና ችግር ሊገጥማት እንደሚችል በቅድሚያ ሊያመላክተን ይችላል።የነዚህ ድርጅቶች የጋራ መመሪያ ወይም ማኒፌስቶ የተዘጋጀው በአንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ስር በተካተተው በኢሕአዴግ በረቀቀው ሕገመንግስት ነው።

## በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው አገራዊና ክልላዊ የፖለቲካ ድርጅቶች

| የፓርቲው ሙሉ ስም | አህጽሮተ-ቃል |
|---|---|
| 1 የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ | ኦብኮ/ክልላዊ/ |

2 የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መኢአድ/አገራዊ/

3 የምዕራብ ሶማሌ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ምሶዲፓ/ክልላዊ/

4 የኦሮሞ ነጻነት አንድነት ግንባር ኦነአግ/ክልላዊ/

5 የሱማሌ ሕዝቦች ነጻነት ግንባር ፓርቲ ሶሕነግፓ/ክልላዊ/

6 የጋሞ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ጋዴህ/ክልላዊ/

7 የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ ሐብሊ/ክልላዊ/

8 የዛይ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ዛሕዴድ/ክልላዊ/

9 የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ ፓርቲ ኢሰዴፓ/ክልላዊ/

10 የቤንሻንጉልና ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ቤጎሕዴአግ /ክልላዊ/

11 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ኢብዴፓ

12 የስልጤ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ ስሕዴአፓ

13 የሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሶሕዴፓ

14 የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ኢዴፓ-መድህን /አገራዊ/

15 የጋራ ፖለቲካ መድረክ ጋፓመ /ክልላዊ/

16 የትግሪ ወርጂ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ ትወብድአፓ /ክልላዊ/

17 ቅይጥ ብሔር ብሔረሰብ አንዲት ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ቅብብአኢዴፓ /ክልላዊ/

18 የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት መአሕድ /ክልላዊ/

19 የዘይሴ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ዘሕዲፓ /ክልላዊ/

20 የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ኢሶዲፓ/ክልላዊ/

21 የኦይዳ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አብዴድ/ክልላዊ/

22 የደንጣ፣ዱባሞ ክችንችላ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ደዱክዴድ /ክልላዊ/

23 የሐረሪ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሐሕዴፓ /ክልላዊ/

24 የኢትዮጵያውያን አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ኢአዴድ/ክልላዊ/

25 የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት ደኢሕዴህ/ክልላዊ/

26 የሀድያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሀብዴድ/ክልላዊ/

27 የከምባታ ሕዝቦች ኮንግሬስ ከሕኮ/ክልላዊ/

28 የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ደኢሕዴን/ክልላዊ/

29 የጌዲኦ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ጌሕዴድ/ክልላዊ/

30 የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ቅንጅት ሶዴሀቅ/ክልላዊ/

31 የኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር ኦአነግ/ክልላዊ/

32 የየም ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የብዴን/ክልላዊ/

33 የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ አብዴፓ/ክልላዊ/

34 የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ኦሕዴድ/ክልላዊ/

35 ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ብአዴን/ክልላዊ/

36 የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ኢሕአዴግ/አገራዊ/

37 የዶንጋ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ዶሕዴድ/ክልላዊ/

38 ሕዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ ሕወሐት/ክልላዊ/

39 የአገው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አሕዴን/ክልላዊ/

40 የስልጤ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ሰብዴን/ክልላዊ/

41 የጠምባሮ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት ጠሕዴህ/ክልላዊ/

42 የባሕር ወርቅ መሰመስ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ባወመሕዴድ/ክልላዊ/

43 የጉራጌ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ጉሕዴድ/ክልላዊ/

44 ሶዶ ጎርደና ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሶጎሕዴድ/ክልላዊ/

45 የኦሮሚያ ነጻነት ብሔራዊ ፓርቲ ኦነብፓ/ክልላዊ/

46 የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ሊግ ኢዴሊ/ክልላዊ/

47 የአንደጋኝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ህብረት እሕዴን/ክልላዊ/

48 የኮንሶ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ህብረት ኮሕዲህ/ክልላዊ/

49 የሸኮና መዥንግር ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ድርጅት ሸመሕዴአድ/ክልላዊ/

50 የኦሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት ኦሕዴህ/ክልላዊ/

51 የሲዳማ አርነት ንቅናቄ ሲአን/ክልላዊ/

52 ባሕረ- ወርቅ መሰመስ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ድርጅት ባመብዴአድ/ክልላዊ/

53 የኢትዮጵያ በርታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ኢበሕዴድ/ክልላዊ

54 የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ወሕዴግ/ክልላዊ/

55 የጋሞ ጎፋ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ጋጎሕዴአ/ክልላዊ/

56 ገዳ ስርዓት አራማጅ ፓርቲ ገስአፓ/ክልላዊ/

57 ዎላይታ ዴርይ የምያ ዋዴየ/ክልላዊ/

58 ዱቤና ደገኒ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ዱደብዴፓ/ክልላዊ/

59 የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት ኢዴህ/ክልላዊ/

60 የዲል ወቢ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ዲወሕዴን/ክልላዊ/

61 የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር አአዴአግ/ክልላዊ/

62 መላው ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መኢዴፓ/አገራዊ/

63 ቀስተ ደመና የኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የማህበረሰብአዊ ፍትህ ንቅናቄ/ቀስተ ደመና ኢትዮጵያ /አገራዊ/

64 የኢትዮጵያ ፓን አፍሪካኒስት ፓርቲ ኢፓአፓ/ክልላዊ/

65 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ኢዴሃህ/ክልላዊ/

66 ኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲአዊ ድርጅት ኦፌዴን/ክልላዊ/

67 የሲዳማ ሃድቾ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሲሀሕዲድ/ክልላዊ/

68 የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ ኢብአፓ/ክልላዊ/

69 የደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች አንድነት ደኢዲሃአ/ክልላዊ/

70 የአፋር ነጻ አውጪ ግንባር ፓርቲ አነአግፓ/ክልላዊ/

71 የመላው ኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ንቅናቄ መኢብን/ክልላዊ/

72 የቤንች ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ቤሕዲድ/ክልላዊ/

73 የኢትዮጵያ ሱማሌ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ግንባር ኢብአዴግ/ክልላዊ/

74 የኦሮሞ ነጻነት ፓርቲ ኦነፓ/ክልላዊ/

75 ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ቅንጅት/አገራዊ/

76 የሸኮና አካባቢው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሸአሕዲድ/ክልላዊ/

77 የሃዲያ ብሔራዊ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሀብአዲድ/ክልላዊ/

78 የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ ኢዲአን/ክልላዊ/

79 የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግሬስ ኦሕኮ/ክልላዊ/

80 ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲ ሉዓላዊነት ዓረና/ክልላዊ/

81 ብርሃን ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ብለለፓ/ክልላዊ/

82 ወለንኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ወቋተሕዴን/ክልላዊ/

83 የኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ ፓርቲ አዲስ ምዕራፍ/ክልላዊ/

84 የአርጎባ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አሕዲድ/ክልላዊ/

85 የሐረሪ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሐዲድ/ክልላዊ/

86 የጋምቤላ ሕዝቦች አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋሕአዲን/ክልላዊ/

87 አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ አንድነት/አገራዊ/

88 የኢትዮጵያ ፍትህና ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ግንባር ኢፍዲሃግ/ክልላዊ/

89 የመላው ኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ መኦዴፓ/ክልላዊ/

90 የአርጎባ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አብዴን/ክልላዊ

91 ኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ ኢራፓ/ክልላዊ/

92 የአፋር ብሔራዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር አብአዴግ/ክልላዊ/

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያስቀመጥኳቸው የፖለቲካ ድርጅቶች የመንግስት እውቅናን አግኝተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩና አሁንም ለምርጫው የቀረቡትንና በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙትን ድርጅቶች እንድታውቋቸውና በተጨማሪም የአገራችን ፖለቲካ ምን ያህል መቀለጃና አደገኛ እንደሆነ እንድትገነዘቡት ሊረዳ ይችላል በማለት ነው።ለጋራ ጥቅም ሲባል የሕዝቦች መደራጀት መልካም መሆኑ ባይካድም ከላይ በተመለከተው መልክ የተደረገው አደረጃጀት ግን ለማን ጥቅምና ዓላማ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል። በስልጣን ላይ ያለው ዘረኛ መንግስት ሕዝቦችን ከፋፍሎ ያሻውን ለማድረግ አመች ሁኔታን ለመፍጠር ያደረገው ተንኮል መሆኑን ለማወቅ የግድ ነብይ መሆን አያስፈልግም። በድርጅት ላይ ድርጅት እየፈጠረ እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ የማድረጉ ዘዴ ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን በቅኝ ገዢዎች የተለመደ የብዙ መቶ ዓመታት የብዝበዛና የጭቆና ዘዴ ነው።በሃይል ስልጣን ይዞ፣ከፋፍሎ መግዛት ከተቻለ መቀጠል ካልሆነ ግን አገራትን መበታተንና ከፋፍሎ ማጋደል የሚለው መመሪያ ቅኝ ገዢዎች ሲጠቀሙበት የኖረ በዓለም ታሪክ ተደጋግሞ የታዬ መሆኑን በአንዳንድ አገራት ላይ የደረሰውን እልቂትና ስብራት ማስተዋሉ ይጠቅማል።በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለው ፣በኢሕአዴግ የሚረጨው የዘርና የክልል ፖለቲካ የሕዝቦች መብትና እኩልነት የሚረጋገጥበት እውነተኛ የዲሞክራሲ አሰራር ሳይሆን ሁሉንም ሊጎዳ የሚችል አደገኛ በማር የተለወሰ መርዝ ነው።

አደገኛነቱ እየታወቀ ለዚህ ሰለባ የሆኑ ድርጅቶች መሪዎችና የብሄር ምሁራን በተመሳሳይ መልክ ለጸረ አንድነት ተሰልፈው ሲታዩ ከኢሕአዴግ ጋር ያላቸው ቅራኔ ከአንገት በላይ እንጂ ከልብ እንዳልሆነ ለመረዳት ይቻላል።የቆሙት ለአንድነትና ለጋራ ጥቅምማ ቢሆን ኖሮ አንግበው የሚንቀሳቀሱበትን የከባቢና የዘር ስም የሚያንጸባርቀውን ድርጅታዊ ስያሜ ቀይረው በፖለቲካ መርሆና መስመር በተካተቱ ነበር።ለስልጣን ደጀን ሊሆን የሚችለው በዘርና በከባቢ መሰለፍ መሆኑን ስላወቁ ምንም ስህተት መሆኑ ቢገባቸውም አቋማቸውን ለመለወጥ ፍላጎት የላቸውም።ብዙ ተወዳዳሪና ተሳታፊ ከሚኖርበት ኢትዮጵያዊነት ይልቅ በጠባቡ መስክ ላይ መሰለፉ ያዋጣናል ብለው ያምናሉ።

በሚካሄደው የምርጫ ቅስቀሳ ተካሮ የሚታየው ትግል በኢሕአዴግ፣በመድረክ(የተለያዩ ዓላማና ፕሮግራም ያላቸው ስምንት ድርጅቶችን ያቀፈ)በኤዴፓ፣በቅንጅት፣በመኢአድ መካከል ሲሆን እነዚህ የተለያዩ የሚመስሉት የፖለቲካ ድርጅቶች የሚከተሉት ርዕዩተ ሲመረመር በሁለት ጎራ ላይ ብቻ የተካተተ ይሆናል።በዘርና በሊበራል የከበርቴ ስርዓት የኤኮኖሚና የፖለቲካ መስመር የሚጠቃለሉ ናቸው።ሁሉም ተቃዋሚዎች ያነገቡትን የግል ዓላማ ጥለው በአንድ የፖለቲካ መስመር ቢሰለፉ ኖሮ ጠንካራ ሃይል ኖሯቸው ገዥውን ፓርቲ ባሸመደመዱት ነበር።አሁን ግን እንደሚታየው ከሆነ እርስ በርሳቸው ሲሻኮቱ ለገዥው ፓርቲ ተንኮልና አመጽ የተመቹ አድርጓቸዋል።የሕዝቡንም እምነት አሳጥቷቸዋል። አንዳንዶቹ በሚያሳዩት የእርስ በርስ ግጭትና ምግባረ ቢስ አድራጎት ሕዝቡ "ካለመዱት መልአክ የለመዱት ሰይጣን ይሻላል" ከሚል የተሳሳተ አቋም ላይ እንዲደርስ አድርጎታል።

በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎች የሚሰማው ደጋፊዬ ተገደለብኝ የሚለው መወነጃጀልና ክስ ወደ ተካረረና ወደ ከፋ ደረጃ ሊያመራ እንደሚችል ምልክቶች ታይተዋል።

የምርጫውን ውጤት ተከትሎ ሊመጣ የሚችል ውዝግብ እንደሚኖር በሕዝብ ዘንድ ስጋት አሳድሯል። በተለይም መንግስት የፖሊስና የጦር ሃይሉን በከተማዎች ውስጥ ማሰባሰቡና ማጠናከሩ ያደረበትን ስጋት ያሳያል።መንግስት በተቃዋሚዎች የቀረበውን አቤቱታ ባልተረጋገጠ ክስ መወንጀል ስለሆነ በስም ማጥፋትና ቅስቀሳ በማድረግ ያስቀጣል፣ጉዳዩ በሚመለከታቸው ድርጅቶች ላይ ክስ ይመሰረታል የሚል ዛቻ ሲሰነዝር በተመሳሳይ ሁኔታ እሱ እራሱ ደጋፊዎቼ ተገደሉብኝ ብሎ ለሚያቀርበው ያልተረጋገጠ ክስና ስም ማጥፋት ግን በተመሳሳይ መልኩ በሕጋዊ መንገድ እንዲታይ ፈቃደኛ አይደለም።ሕጉ በሚቀናቀኑትና በማይደግፉት ላይ እንጂ በራሱ ላይ የማይሰራ፣ እራሱን የሚንከባከብበት መሳሪያ መሆኑን በተደጋጋሚ እየፈጸመ ነጻ በሆነባቸው ብዙ ጥፋቶቹ ለመረዳት ይቻላል።

የተቀዋሚውን ጎራ በተመለከተ በቁጥር እንጂ በጥራት የሚያስተማምኑ አይመስሉም። የዬአንዳንዶቹ ፓርቲዎች ፍላጎት ካለው መንግስት ጋር ስልጣን ለመጋራት እንደሆነ በይፋ ተናግረዋል።የሌሎቹም መመሪያቸው የኔዎሊበራል መርሆ እንደሆነ በኩራት ገልጸዋል።ለምን ግን አንድ ላይ በአንድ ፓርቲ ስር እንደማይሰለፉ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው።የኔዎሊበራል አቋም ሁሉም ነገር ለሽያጭ የሚል ለከበርቴው ስርዓት ያጎበደደ፣ብሔራዊ ስሜት የጎደለው፣ለሰፊው ሕዝብና ለደሃው ደንታ የሌለው ሲሆን በአውሮፓና በሌላውም አገራት በሚታየው የኤኮኖሚና የሶሻል ቀውስ ዋና ተጠያቂ የሆነ፣ችግር በችግር ላይ የሚወልድ እንጂ መፍትሄ የማያመጣ፣በዴሞክራሲና በነጻ ገበያ ስም አገራትን ለዘረፋ አሳልፎ የሚሰጥ የአቀባባይ ከበርቴ ንድፈ ሃሳብ ነው።በቃላት ኔዎ ሊበራሊዝምን እንከተላለን የሚሉት ወገኖች ከቃሉ ባሻገር ምን ይዘት እንዳለው በቅጡ የተረዱትና የሚያውቁት አይመስልም፤እንደው በጭፍኑ ከምዕራቡ ዓለም ጋር የተወዳጁ ወይም በአንድ ሰልፍ የሚሰለፉበት መስሏቸው ድጋፍ መሰብሰቢያ ዋና መሳሪያ አድርገው ሳያውቁ የተቀበሉት መርሆ ይመስላል።ኢህአዴግን ኮመኒስት ነህ እያሉ ይከሱታል።ስለ ኮሚኒዝም ያላቸው ግንዛቤ በጣም የተሳሳተና የተዛባ መሆኑን አልተረዱትም።ኢሕአዴግ ዘረኛ፣ጸረ አንድነትና ሰላም፣አገሪቱን ለመበታተን ታጥቆ የተነሳ፣የኢትዮጵያን መኖር ለማይሹ የውጭ ሃይሎችና ታሪካዊ ጠላቶቿ ጥቅምና ፍላጎት የቆመ፣ የማታ ማታ አገሪቱን አተረማምሶ ክልሉን ገንጥሎ ለመኖር "አብዮታዊ ዴሞክራሲ"በሚል እራሱ በፈጠረው ፈሊጥ እያምታታና እያመቻቸ የሚመራ አገር በቀል ጠላት ነው።

በሁለቱም ጎራ ለምርጫው የሚደረገው ቅስቀሳ በሰፊው ቀጥሏል።በከተማዎች በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ የምርጫ ሰሌዳና ፖስተሮች የተለጠፉ ሲሆን በከፍተኛ ወጭ ጥራትና ብዛት ያለው ማስታወቂያ የለጠፈው በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ነው። ለዝግጅቱ ከሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር በላይ ወጭ መደረጉ ሲገለጽ ኢሕአዴግ ከፍተኛውን ድርሻ እንደወሰደ በይፋ ይነገራል። በተጨማሪም ከመንግስት ካዝና ለመጠቀም የሚያግደው የለም።ሁሉ በጄ ሁሉ በደጁ ነው።በጥቅማ ጥቅም ብዙ አጫፋሪዎችንና ደጋፊዎችን ለማሰለፍ ችሏል።

ወጣም ወረደም ምርጫውና ውጤቱ ሀቅና ሕግ የማይከበርበት ለመሆኑ የሚታዩት አዝማሚያዎች ያረጋግጣሉ።ሕዝቡ ድምጹን ሳይሰጥበት በቅድሚያ በዚህ ከተማና ክልል ውስጥ እኔ አሸንፋለሁ የሚለው የተወዳዳሪ ድርጅቶች ፉከራ የደጋፊን ሞራል ለመጠበቅ

መስሎ ቢታይም ከምርጫው ማግስት ጀምሮ ለሚቀሰቀሰው ግርግር የመዘጋጃ ጥሪ እንደሆነ ከወዲሁ መታወቅ አለበት። የገዢው ፓርቲ ሽንፈትን ላለመቀበል ታጥቆ የተነሳ ይመስላል።በውድም ሆነ በግድ ስልጣንን አሳልፎ ላለመስጠት የማያደርገው አይኖርም፤ ድምጽ ከመገልበጥ እስከ አመጽ ድረስ።

በተቃዋሚ ካምፕ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ከነ አቶ መለስ ጋር ያላቸው ጠብ የስልጣን እንጂ የአላማ ልዩነት አይደለም።ለብዙ ዓመታት በአንድ አላማ ተሰልፈው በስልጣን ላይ የነበሩ የአንድ ድርጅት አባላት ናቸው።በከባቢና በዘር ላይ በተመሰረተው የፖለቲካ እምነታቸው አይለያዩም።የአሁኑ መለያየታቸው ጊዜያዊና ሊታረቅ የሚችል ልዩነት ነው።አህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም እንደሚሉት ነገር ነው።

በቅርቡ በድርጅታቸው ጋዜጠኛ የቴሌቪዥን የጥያቄ ፕሮግራም ለአቶ መለስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበው ነበር።ጥያቄዎቹ  በተለይ በሃሰብ ወደብ፣ተቃዋሚዎች በኤርትራ መንግስት ድጋፍ ሚያካሂዱትን የትጥቅ ትግል እንዲሁም አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ የተሰ`ነውን የብሔሮችን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት ያካተተ ነበር።አቶ መለስ ስለ ሃሰብ ወደብ ጥያቄ የሰጡት መልስ ከአንድ አገር በተለይም ወደቧን ከተነፈገች አገር መሪ የሚጠበቅ አልነበረም።የጥያቄው መነሳት እራሱ ደም ስራቸውን አቁሞታል።ከአቶ ይሳያስ አፈወርቂ በላይ የአሰብን ወደብ ኤርትራዊነት አክርረው ተናግረዋል።ኢትዮጵያ በጎረቤት አገሮች ወደብ ለመጠቀም የሚያስችላት እድል ይኖራል እንጂ ተመልሳ የወደብ ባለቤት አትሆንም፣ያለቀለት ጉዳይ ነው ብለዋል።የኤርትራም ሕዝብ የነበረውን ነጻነት ተገፎ፣ባንዲራው ተቀዶ፣ፓርላማው ተበትኖ በጉልበት እንዲቀላቀል የተደረገ፣ በጭቆና ምክንያት ተማሮና ተንገሽግሾ ነጻ የወጣ ሕዝብ ነው በማለት የፈጸሙትን ስህተትና በአገርና በሕዝቦች ላይ ያደረሱትን በደል ታሪካዊ መልክ ለመስጠት ሞክረዋል። በስከጀርባ ግን የትግራይና የኤርትራ ደጋ ክፍል ተዋህዶ በትግረ ትግርኛ በሚል መርሆና የቆዬ ምኞት(እንግሊዞችም ከፌዴሬሽኑ በፊት ይገፉበት የነበረ አማራጭ ነበር) ለማጣመርና በአንድ መንግስት ስር ለማዋሃድ የቤት ስራው በሚስጥር ቀጥሏል።ይህ በተግባር ከተገለጸ የመሃል አገሩ እጣ ፈንታ ምን ይሆናል ?ብሎ መጠየቅና መልስ መስጠት የሁሉም ኢትዮጵያዊ አንገብጋቢ ተግባር መሆን ይኖርበታል።ተዘናግቶ ነገራትን በቀላሉ ማየትና መዘግየት የኋላ ኋላ ቁጭ ብለው የሰቀሉት ቆመው ለማውረድ እንደሚያዳግተው ከባድ ስራ ወይም ጅብ ከሄደ በኋላ እንደሚጮኸው ውሻ እንደ መሆን ይቆጠራል።አገር ቢፈራርስ ሁሉም ይጎዳል እንጂ ተጠቃሚ አይሆንም።ተለያይቶ ለመኖር ሽር ጉድ የሚሉት ሁሉ ከማያውቁትና ካላሰቡት መከራ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ በቅድሚያ ሊገነዘቡት ይገባል።የብዙሃኑ ፍላጎት መለያየትና መገነጣጠል አይደለምና።አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝን በተመለከተም የሰጡት መልስ ከአንድ አገር መሪና ፖለቲከኛ የሚጠበቅ አይደለም።እንግሊዝ አስር ሽህ ኪሎ ምትር እርቃ በቅኝ ግዛት የያዘችውን መሬት አለቅም ብላ ከአርጀንቲና ጋር ተዋግታ የማይገባትን መብት ስታስከብር፣ ሽህ ኪሎ ሜትር ከክልሏ እርቆ በሜዲትራንያን ባህር ላይ የሚገኘውን የጅብራ አልታርን ኮረብታማ ደሴት በቁጥጥሯ ውስጥ አስገብታ ማን አለብኝ ስትል፤ቻይናም ከስልሳ ዓመታት በፊት ከግዛቷ ተገንጠሎ ነጻነቱን አውጆ የኖረውን አገር ለማቀላቀል ጥረት ስታደርግ የኢትዮጵያ መሪ ነኝ

የሚሉት አቶ መለስ ግን የሚከተሉት መስመር ጣሊያኖች በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት በከባቢው ላይ ከነበራቸው አቋም በብዙ መልኩ ይመሳሰላል።

የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱትን ተቃዋሚ ሃይሎች በሚመለከት ጋዜጠኛው ተቃዋሚዎቹ በኤርትራ መንግስት እየተረዱ በመታገላቸው ለምን ይወነጀላሉ?ኢሕአዴግስ ከኤርትራ ጋር ተባብሮ ታግሎ አይደለም ወይ ለስልጣን የበቃው ሲል ላቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣ እኛ ከኤርትራ ጋር ተባብረን ያደረግነው ትግል ለነጻነትና ለብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ነው፤ተቃዋሚዎቹ ግን ይህን የሚጻረርና የተገኘውን የዲሞክራሲ መብትና ድል የሚቀለብስ ጸረ ሕዝብ ትግል ነው በማለት ኮንነውታል።ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ይሏል ይህ ነው።

በቆየሁበት ጊዜ የታዘብኩት ሌላው ነገር ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተማሪዎች መካከል ተከስቶ የነበረው ግርግር ነው።ለግርግሩ መነሻ የሆነው የአንድ ሞባይል ቴሌፎን መጥፋት እንደሆነ በመንግስት የተሰጠበት ችግር እውነቱ ከዚያ የተለየና ለረጂም ጊዜ ተጠራቅሞ የፈነዳ የፖለቲካ ይዘት እንዳለው ካገኘሁት የውስጥ መረጃ ለመገንዘብ ችያለሁ።

ቀደም ሲል የትንሳዔ በዓልን ምክንያት በማድረግ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙት ከልዩ ልዩ ብሔራት የተውጣጡት ተማሪዎች በስምምነት(እነዳለመታደል ሆኖ የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ሳይቀር በክልልና በዘር ተዋረድ የተሰለፈ ስለሆነ)በአማርኛ ፊደላት"እንኳን ለትንሳኤው በዓል በደህና አደረሳችሁ" የሚል የመልካም ምኞት መግለጫ በመግቢያ በር ላይ በመስቀላቸው ጥቂት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች፣በተለይም የኦነግ ደጋፊ የሆኑት በመቃወም የተሰቀለው ጽሁፍ እንዲወርድና በኦሮምኛ ቋንቋ የላቲን ፊደላት እንዲተካ በተጨማሪም ሰላምን ለማውረድ ሲባል የተሰቀለውን ለማውረድ ቢስማሙም መውረዱ ብቻ ሳይሆን የተጻፈበት ጨርቅ እንዲቃጠል በመጠየቃቸው ገደብ ያለፈው ጥያቄና ማን አለብኝ ትቢት የቀሰቀሰው ውዝግብ እንደሆነ የሰበሰብኩት የቃል መረጃ ያረጋግጣል።በስተ ጀርባ አንዳንድ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ችግሩ እንዲባባስ ድጋፍና ከለላ ይሰጡ እንደነበረ ተጠርጥረዋል። ሌላው ቢቀር ድርጊቱ ትክክል አለመሆኑን በሚናገሩትና እርስ በርሳቸው በሚግባቡበት ቋንቋ ሰላም እንዲወርድና ጠቡ እንዲበርድ ማድረግ ይችሉ ነበር።ያንን አለማድረጋቸው ግን የዝምታ ድጋፍ እንደሰጡ ይቆጠራል።ችግሩ በዚህ ብቻ አላቆመም።የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚለውም አጠራር ፊንፊኔ ዩኒቨርሲቲ መባል ይኖርበታል በማለት ሕገ ወጥ ማህተምና ካናቴራ በማሳተም እንደሚንቀሳቀሱ ለማወቅ ተችሏል።

ሌላው በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ያለው ስጋት በባህል ትእይንት ስም በብዛት ወደ ውስጥ ሰርጎ እንዲገባ የተደረገው በተማሪዎች እጅ ውስጥ የሚገኘው ጩቤ፣ጎራዴ፣ጦርና ጋሻ በውጭና በውስጥ የፖለቲካው ፋክክርና ትንቅንቅ እየከረረ ከሄደ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ነው።አንድ ዩኒቨርሲቲ የዕውቀት እንጂ የጦርነትና የግጭት ሜዳ አለመሆኑ ሲታወቅ፣በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው ጤነኛ ያልሆነ፣የዘር ፖለቲካ መኖሩ ሳይዘነጋ የዚህ አይነቱ ሁኔታ እንዲፈጠር ማመቻቸት እራሱን የቻለ ወንጀል ነው። ለደረሰውና ሊደርስ ለሚችለው ቀውስና አደጋ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ሊጠየቅበት ይገባል።በግርግሩ ወቅት ቁጥራቸው ያልታወቀ ተማሪዎች ታፍሰው የት እንደደረሱ

አይታወቅም።አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ተማሪዎች ከፍተኛ አደጋ እንደደረሰባቸው በሰፊው ይነገራል።ስለተቀሰቀሰው ችግር አንድ ግለሰብ ተማሪ የሰጠውን ማብራሪያ እንዳለ፣ሳይጨመርና ሳይቀነስ ሳይሻሻልም ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁና በትእግስት እንድታነቡት እጠይቃለሁ።

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደው የብሔር ግጭትና የረጂምና የአጭር ጊዜ ምክንያቶች

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የብሔር ብሔረ ሰቦችን ስብስብ የያዘ በመሆኑ "ትንሿ ኢትዮጵያ"የሚል ቅጽል ስም በተለያዩ አካላት ተሰጥቷታል፤ቢሆንም ግን መቻቻልን እንደሚያስተናግድ ሁሉ የተለያዩ ልዩነቶችና የግል ፍላጎቶች በሰፊው ይንጸባረቃሉ።ይባስ ብሎም ያላዋቂነትን አጉልተው የሚያሳዩ በርካታ ነገሮች በተለያዩ አካላት ይራመዳሉ።በያዝነው የትምህርት ዘመን (2002 ዓ.ም.)ማራጫን በማስታከክም ሆነ በሌላ ምክንያት ወገንተኛዊነትን የሚያንጸባርቁና ክፍፍል የሚያስነሱ አጀንዳዎች በተደጋጋሚ ሲራገቡ ይስተዋላል።ከነዚህም ጉዳዮች አሁን ላለንበት የቡድን/የብሔር ግጭቶች ዋነኛ ምክንያቶች ሆነዋል።ለዚህም ሚያዝያ 23-2002 ዓ.ም. ቅዳሜ ማታ ከ23.00 -06፡00 ሰዓት በትግራዮችና በኦሮሚያ ተወላጆች መካከል የከረረ የቡድን ግብግብና ድብድብ ተከሂዷል።በቀጣይ ከሁለት ቀናት በኋላ በሚያዝያ 26-2002 ማክሰኞ ተመሳሳይ ግጭት ተነስቶ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ለጉዳት የተዳረጉ ሲሆን ከትግል ለመሸሽ በመኖሪያ ህንጻቸው የተቀመጡ ተማሪዎችም የፌዴራል ፖሊስ ለሚያደርገው ክትትል ሲባል እስከ ሌሊቱ 11 ሰዓት ድረስ ውጭ ላይ ሲፈተሹ ፣ቃል ሲሰጡና የቪዲዮ ቀረፃ ተደርጎባቸው በማስጠንቀቂያ የፈረሙ ከ1600 በላይ የሚሆኑ ሲሆኑ በተጨማሪ የችግሩ አነሳሽ ይሆናሉ ተብለው የተጠረጠሩ ተማሪዎችም በእስረኛነት ተወስደዋል።ከፍተኛ የሆነ የሰውና የግቢውን ንብረት ውድመት ምክንያት በሁለት መልክ የሚታዩ ሲሆን እነዚህም የአጭርና የረጅም ጊዜ ምክንያቶች ናቸው።

የረጅም ጊዜ(የቆዩ) ምክንያቶች

1ኛ.የትምህርት ሚኒስቴር የተማሪዎች አመዳደብ የብሔር ተጽእኖ አለመመጣጠን፣ይህም ማለት የትግራይና የኦሮሚያ ተማሪዎች ከሌሎቹ በተለዬ ሁኔታ ቁጥራቸው መብዛቱ።

2ኛ.የዩኒቨርሲቲው አስተዳደራዊ ችግሮች

ሀ.የዲሲፒሊን ኮሚቴ አለመኖርና ተግባሩን በአግባቡ አለመወጣት፣በሃይማኖትም ዙሪያ ላይ ያለውን ግጭት ለመፋታት ፋይዳ ያለው ስራ አለመስራት፤ለምሳሌም የፋሲካ በዓል አከባበር

3ኛ.በመመረቂያ ቲ- ሸርቶች ላይ የሚወጡ ጽሁፎችና ምልክቶችን አለመቆጣጠር።ለምሳሌም የኦሮሚያ ተወላጆች የሆኑት የዩኒቨርሲቲውን ስም ቀይረው ፊንፊኔ ማለትና የዛፍ አርማ ማተም።

4ኛ.የተማሪው ጥያቄዎች በተገቢው ሰዓትና መንገድ አለመመለስ።

የአጭር (የቅርብ)ጊዜያት ምክንያቶች

1ኛ.በሞባይል ቴሌፎን መጥፋት ምክንያት ሚያዝያ 23 ቀን ከቀኑ ስድስት ሰዓት አካባቢ በሁለት ብሄር ተማሪዎች መካከል የተነሳው ጠብ ወደ ብሔር ጠብ መቀየሩ።

2ኛ.በዚያው እለት በተፈጠረው ችግር ዩኒቨርሲቲው በአስቸኳይ የጥበቃ ሃይል አለማዘዙና ተማሪዎችን ሰብስቦ አለማናገሩ ለጠቡ መስፋትና እድሜ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

3ኛ.በየብሔሮቹ ውክልናውን ወስደው ግጭት የሚያነሳሱትን ለይቶ አለማውጣት አብይ ምክንያቶች ናቸው።በዚህም ምክንያት ግቢው ብዙ ንብረቶችን ያጣ ሲሆን ተማሪዎችም ብዙ ፈተናዎች ደርሶባቸዋል።በአሁኑም ሰዓት ግቢው ሊረጋጋ የቻለው በፌደራል ፖሊስ ሃይል ሲሆን እነሱ የሚወጡ ከሆነ አደጋው ያንዣበበ መሆኑና እንደሚያገረሽበት ብዙ ምልክቶች ያሳያሉ።

ከዚህ በላይ ለማቅረብ የሞከርኩት በአገር ውስጥ በቆየሁበት አጭር ጊዜ ውስጥ የታዘብኩት ሲሆን ከዚህ በታች ደግሞ በተለመደው የታሪክ ማህደር አምድ ላይ አረመኔው መንግስቱ ሀ/ማርያም እንዴት ዚምባብዌ እንደገባ ተገዶ በረራውን የፈጸመው ፓይለት የሰጠውን የግል ምስክርነት ለማቅረብ እወዳለሁ።ከፓይለቱ ጋር በአንድ መስሪያ ቤት ውስጥ የሰራን ሲሆን አየር መንገድ ከመዛወራቸው በፊት በኮሎኔል ማዕረግ ምክትል የቤዝ ኮማንደር ነበሩ።አሁን ግን በሕይወት አይገኙም።

ግንቦት 14 ቀን 1983 ዓ.ም.

ጉዳዩ፡-ተገዶ መብረር/የበረራ መስመር ቁጥር 8107

ግንቦት 12 ቀን 1983 ዓ.ም. ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ከፍላይት ኮንትሮል ስልክ ተደውሎ ነገ ከፍተኛ ባለስልጣን ይዘህ ጂማ ስለምትበር ከጠዋቱ 0600ሰዓት እንዳመለክት ተነገረኝ።ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ ም.05፡30 ሰዓት የመ/ቤት መኪና ተልኮ ወሰደኝ።0600 ፍላይት ኮንትሮል ሳመለክት የ 7 ሰዓት ተኩል ነዳጅ እንድሞላ በቀኑ ከነበረው ተረኛ ተነገረኝ።እኔም ጅማ ነዳጅ ስላለ ከ4 ሰዓት የበለጠ ነዳጅ እንዳይሞላ /እንደማልሞላ ነገርኩት።ትንሽ ከቆዬን በኋላ የበረራ መስመሩ ተለውጦ ከአ.አ.ብላቴን ፡ከብላቴን አስመራ ፡ከአስመራ አዲስ አበባ እንደምበር ስለተነገረኝ ረዳት አብራሪውን ከአ.አ ብላቴን፡ከብላቴን አስመራ፡ከአስመራ አ.አ.በካርታ ላይ እንዲያሰምርና የበረራው ሰዓትም ስንት እንደሚፈጅ ስለነገረኝ ከነመጠባበቂያው የ7 ሰዓት ተኩል ነዳጅ እንዲሞላ ነገርኩት።

ከዚያም ወደ አውሮፕላኑ ሄደን ነዳጁን ሞልተን ስንጠብቅ ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ ፕሬዚደንት መንግስቱ ሃይለማርያም በሁለት መኪናዎች ታጅበው ወደ አውሮፕላኑ መጡና ከመኪናው ወርደው አጃቢ ወታደሮች ጋር ወደ አውሮፕላኑ ገቡ።

እኔም ከአውሮፕላኑ ውጭ ስለነበርኩ ጓድ መንግስቱ ገመቹ ለመሸኘት መጥተው ስለነበር እሳቸውን የት ነው የምሄደው ብዬ ስጠይቃቸው መጀመሪያ ብላቴን ነው ከዚያ በኋላ ግን ፕሬዚዳንቱ ወደሚያዙህ መሄድ ነው ብለው ነገሩኝ።እኔም እረዳት አብራሪዬና ከሁለት የበረራ መካኒኮች ጋር ወደ አውሮፕላኑ ገብተን ሞተር አስነስተን ከቦሌ 0835 ሰዓት ተነስተን ወደ ብላቴን ቀጠልን።በበረራ ላይ እንዳለን የበረራ አስተናጋጅ 7 መንገደኞች እንዳሉ ነገረኝ።

በ09፡10 ሰዓት ብላቴን ለማረፍ ስንወርድ የበረራ አስተናጋጅ ፕሬዚደንቱ ያጠሩሃል ብሎ ነገረኝ።እኔም ለረዳት አብራሪው ሰጠሁና ወደ ፐርዚደንቱ ሄድኩ።እሳቸው ዛሬ በጣም አስቸኳይና የማይቀር ስብሰባ ናይሮቢ ስላለኝ ዛሬውኑ ናይሮቢ ደርሼ ወደ ኢትዮጵያ ስለምመለስ ወደ ናይሮቢ ቀጥል አሉኝ።እኔም የበረራ ካርታና የአፕሮች ቻርት ስለሌለኝ ለመብረር አስቸጋሪ ነው ስላቸው ይኽ የማይቀር ጉዳይ ስለሆነ በምትችለው ሁሉ አድርገህ መቀጠል አለብህ አሉኝ።ወደ ኮክፒት ገብቼ ካርታውን ስፈልግ ከ8 ዓመት በላይ ከበረራ ቦርሳዬ ውስጥ የነበረች አንድ አሮጌ ኤር ወይም ቻርት አገኘሁና በረራውን ቀጠልን። ከዚያም በኋላ ተጠራሁና ስብሰባው በጣም ሚስጥር ስለሆነ ምንም የራዲዮ ግንኙነት እንዳታደርግ አሉኝ።እኔም እሽ ብዬ ወደ በረራ ክፍሌ ተመለስኩ።በረራውን በመቀጠል ናይሮቢ ለመድረስ 1 ሰዓት ተኩል ሲቀረኝ አንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን የበረራ መስመር 825 የሆነ ከናይሮቢ ጋር ሲነጋገር ሰማሁና እረዳት አብራሪዬን እንዲጠራው ነገርኩት።ከዚያም ግንኙነት ካገኘን በኋላ ወደ ሌላ መነጋገሪያ መስመር ለውጠን በኢትዮጵያ ፕሬዚደንት ተገድጀ ወደ ናይሮቢ እንደምበርና የናይሮቢ የበረራ መረጃዎች እንዲሰጡኝ ነገርኳቸው።እነሱም ጠቃሚ የሆኑትን የበረራ መረጃዎች ሰጡኝ።ከዚያም አንድ ሰዓት ለመድረስ ሲቀረኝ ከናይሮቢ የበረራ ተቆጣጣሪ ጋር ግንኙነት አደረግን፣ለመድረስ 30 ደቂቃ ሲቀረን የበረራ ተቆጣጣሪው ጠራኝና የማረፍ ፈቃድ አለህ ወይ?ብሎ ሲጠይቀኝ እኔ ታዝዤና ተገድጄ ነው የመጣሁ እና የማውቀው ነገር የለም አልኩት።ከዚያ በኋላ በአስተናጋጅ በኩል ችግሬን ለፕሬዚደንቱ እንድነግራቸው ካደረኩ በኋላ ቪ.አይ.ፒ. በረራ መሆኑና በናይሮቢ የኢትዮጵያ አምባሳደር ወደ አውሮፕላን ማረፊያ እንዲመጣ ብላችሁ ንገሩ አሉ ተባልን።እኛ የበረራ ተቆጣጣሪው የከፍተኛ ባለስልጣን በረራ መሆኑን ናይሮቢ ያለው የኢትዮጵያ አምባሳደር ወደ አውሮፕላን ማረፊያ እንዲመጣ እንዲነግሩት ነገርናቸው።ከዚያም በረራውን በመቀጠል በ12፡25 ሰዓት ናይሮቢ አረፍን።ካረፍን በኋላ የሚቀበላቸው ሰው ስላጡ አውሮፕላኑ ውስጥ 40 ደቂቃ ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያ አምባሳደር ረዳት የተባለ አንድ ሰው መጣና ተነጋግረው ተመለሰ።ከ30 ደቂቃ በኋላ 2 መኪናዎች መጡና ፕሬዚዳንቱና 4 ወታደሮች ሲወርዱ 2 ወታደሮች ለጥበቃ ትተው እኛንም ሳያነጋግሩን ተለያየን።እኛም እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ብንጠብቅ ምንም ሰው ስላጣን በኢትዮጵያ አየር መንገድ መኪና ለመሄድ ወሰንን።ወታደሮቹን ከእኛ ጋር ወደ ሆቴሉ እንዲሄዱ ብንጠይቃቸው እኛ አንሄድም ፣አውሮፕላኑን እንድንጠብቅ ስለታዘዝን ያለ ፕሬዚደንቱ ትዕዛዝ ማንም መነቃነቅ አይችልም ፣ለመነቃነቅ ከተሞከረ አውሮፕላኑንም እኛም እዚሁ እናልቃለን ስላሉን እነሱን ትተን ወደ ሆቴሉ ሄድን።ከምሽቱ 2 ሰዓት ተኩል አካባቢ የኢትዮጵያ አምባሳደር ረዳት የተባለው ከሌሎች ሰዎች ጋር ሆቴል መጣና ፕሬዚደንት መንግስቱና አምስት ወታደሮች ወደ ሀራሬ እንደሄዱና አንድ አብሮ የነበረ ሻለቃ አልሄድም ብሎ እንደቀረና ከእኛ ጋር ወደ

ኢትዮጵያ እንድንመልሰው ነግሮን ሄደ።በ14/9/83 ዓ.ም.እኛ የቀረውን ሻለቃ ይዘን ከናይሮቢ 07፡25 ሰዓት ተነስተን አዲስ አበባ በ 11፡00 ሰዓት በደህና አርፈናል።

ካፒቴን መኮንን አደላ

ከዚህ በላይ እንደተመለከታችሁት ያ፣አንድ ጥይት እስኪቀረኝ ድረስ ለአገሬ እታገላለሁ በመጨረሻውም እሰዋላታለሁ እያለ ሲፎክር የነበረ ጨካኝ አረመኔ ለራሱ ደህንነት ሲል የአገርና የወገኑን ክብርና ጥቅም አሳልፎ በመስጠት ታሪክና ትውልድ የማይረሳው በደል ፈጽሞ በውጭ ሃይሎች በተዘጋጀለት መንገድ አገሩን ጥሎ እንዴት እንደወጣ የቀረበውን አንደኛ ደረጃ የያዘ የምስክር ቃል ነው።ውሎ ቢያድርም ለፈጸመው ኢሰብአዊ አድራጎት፣ጭፍጨፋና ክህደት ተገቢውን ፍርድ በኢትዮጵያ መሬት ላይ እንደሚያገኝ ጥርጥር የለውም።ያንን ለመስማትና ለማየት ጊዜው እሩቅ አይሆንም።

## የዘረኞችን ፖለቲካ በመቃወም በአገራችን ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለማሶገድ  እንተባበር!!

## የዘር ፖለቲካ መጥፊያችን ነው!!

## ሰላምና አንድነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁን!!

## አገሬ አዲስ፣ሆላንድ